# 3.

# በማ.ፕ.ት አሰራር በማህበረሰብ ደረጃ የሚፈጸም ግዢና የውል ስምምነት

# (Community Procurement and Contracting in CMP)

# 3. በማ.ፕ.ት አሰራር በማህበረሰብ ደረጃ የሚፈጸም ግዢ እና የውል ስምምነት (Community Procurement and Contracting in CMP)

## 3.1 የትግበራ ፕሮጀክት ኡደት (The Implementation Project Cycle)

- ከማስተዋወቅ እስከ የገንዘብ ውል ስምምነት መፈራረም ድረስ ያሉት የፕሮጀክት ኡደቶች የዝግጅት ምዕራፎች ሲባሉ የፕሮጀክቶች ግንባታ እና ተዛማጅ ጉዳዮች የሚከናወኑበት ኡደት ደግሞ የትግበራ ኡደት/ምዕራፍ ይባላል::

- የትግበራ ፕሮጀክት ኡደት የሚከተሉት ዋና ዋና ንኡስ ኡደቶች ይኖሩታል::
  - የጨረታ ሂደት (ግዢ)ና የውል ስምምነት መፈራረም (Tendering/Procurement and Contracting)
  - ግንባታ (Construction)
  - ክትትል (Supervision)
  - ግንባታው የተጠናቀቀ የውሃ ጣቢያ አገልግሎት ማስጀመሪያ ስነስርአት( Project completion ceremony)

- ከላይ ከተጠቀሱት ንኡስ ኡደቶች በተጨማሪ :-

  1. ለፕሮጀክቱ ማከናወኛ በተለያየ የግንባታ ደረጃዎች ወቅት ለዋ.ሽ.ኮ.ው ገንዘብ ይተላለፋል ዋ.ሽ.ኮ.ውም ክፍያዎችን ይፈጽማል::
  2. ኮሚቴዎችም ገንዘቡም የተጠቀሙ ሂሣቡን ያወራርዳሉ:: በወረዳው በሚገኘው የብድርና ቁጠባ ተቋም /ለምሳሌ ምአማራ አ.ብ.ቁ.ተ/ ከማ.ት.ፕ የሚመደበውን የፕሮጀክቱን ገንዘብ ማንቀሳቀሻ የተከፈተው የባንክ ሂሳብ እንዲሁም በዋ.ሽ.ኮ.ው አማካኝነት በውሃ ጣቢያው ስም የተከፈቱት አካውንቶች አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት በወረዳ ገንዘብና ፕላን ጽ/ቤቶች ኦዲተሮች ወይም/ እና የክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰየመው የውጭ ኦዲተር አማካኝነት የሂሣብ ምርመራ (Audit) ይደረጋሉ::

## 3.2 ግዢ እና የውል ስምምነት መፈራረም (Procurement and Contracting)

- በማ.ፕ.ት አሰራር በግንባታ ሂደት ወቅት ግዢና የውል ስምምነት መፈራረም የሚፈጸመው በማህበረሰቡ (በህብረተሰቡ) ሲሆን ይህም ሀላፊነት የተሰጠው:-
  - ለማህበረሰብ አገልግሎት ለሚሰጡ የውሃ ጣቢዎች በውሃ ንጽህናና ሀይጅን ኮሚቴው (ዋ.ሽ.ኮ) ፣
  - ለትምህርት ተቋማት አገልግሎት ለሚሰጡ የውሃ ጣቢዎች የወላጅ መምህር ህብረት (ወ.መ.ህ) ፣
  - ለጤና ተቋማት አገልግሎት ለሚሰጡ የውሃ ጣቢዎች የጤና ኮሚቴ (ጤ.ኮ) ናቸው::

### 3.2.1 በማህበረሰብ ደረጃ ግዢ መፈጸምና ውል መፈራረም ለምን አስፈለገ (Why Community Procurement and Contracting) ?????

- በማህበረሰብ ደረጃ ግዢ መፈጸምና ውል መፈራረም ያስፈለገው የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል ተብሎ ስለሚታመንበት ነው::

1. መንግስት አየተከተለ ላለው የልማት ስልት/ላልተማከለ አስተዳደር (Decentralized Management) ምላሽ ስለሚሰጥ፣
2. ተጠቃሚው ማህበረሰብ በስራውና በሚመደበው በጀት ላይ የሚኖረውን ሀላፊነት ለማሳደግ፣ በዚህም ምክንያት በፕሮጀክቱ ላይ የሚኖረውን የባለቤትነት ስሜት ለማዳበርና የፕሮጀክቱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ፣
3. ለልማት የሚውሉ ሀብቶችን ቀጥታ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲደርሱ ለማድረግ፣

4. በህብረተሰብ ደረጃ አቅምን ለመገንባትና በራስ የመተማመን/በራስ ሃሳብ የመመራትን ስሜት ለማዳበር/ እንዲኖር ለማድረግ፣

5. ለታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ኢኮኖሚውን ሊደግፉ የሚችሉ የስራ እድሎችን ለመፍጠር (ለምሳሌ ለአርቴፊሻኖች፣ አነስተኛ አቅም ላላቸው የእቃ ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን አቅራቢዎች ወዘተ...) ዋና ዋና ዎቹ ናቸው::

## 3.2.2 በማንኛውም የግንባታ ስራ ወቅት ሊኖሩ የሚችሉ የግዢ /የውል አይነቶች

ማንኛውንም የግንባታ ስራ ለማከናወን የሚረዱ መሳሪያዎችን፣ ቁሳቁሶችን እና አገልግሎቶችን (የሰው ሃይል፣ ትራንስፖርት ኪራይ ወዘተ...) ገዢን ለማከናወን ከሚከተሉት ከሶስቱ በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን በመጠቀም ግንባታው ሊከናወን ይችላል::

1. **<u>የስራዎች ግዢ (Procurement of Works)</u> የምንለው /የሰው ሀይል፣ ቁሳቁሶችን እና መሳሪያዎችን በማቅረብ ግንባታውን ለሚያከናውን ግለሰብ/ ድርጅት ውል ሲሰጥ ነው::**

   - ይህ የግዢ አይነት ተግባራዊ የሚሆነው ግንባታውን ለሚያከናውነው ባለሙያ ወይም ተቋራጭ ለስራው የሚስፈልገውን ጉልበት (የሰው ሃይል)፣ የግንባታ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በማቅረብ ግንባታውን እንዲያከናውን ስናደርግ ነው::

2. **<u>የአገልግሎቶች ግዢ (Procurement of Services)</u>**

   - ይህ ግዢ የሚያጠቃልለው ለግንባታው ስራ የሚያስፈለጉ ጉልበት (የሰው ሀይልን) በማቅረብ (እቃ ማቅረብን ሳይጨምር) ስራዎችን ሊያከናውኑ የሚችሉ ግለሰቦች/ድርጅቶች፣ ለግንባታ ስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ሊያከራዩና ሊያጓጉዙ የሚችሉ ግለሰቦችን/ድርጅቶችን ስንቀጥር ነው:: በዚህ

የግዢ አይነት ወቅት ለግንባታው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የሚቀርቡት ሌላ የግዢ (የእቃዎች ግዢ) ዘዴን በመጠቀም በባለቤቱ ይሆናል።

## 3. <u>የእቃዎች ግዢ (Procurement of Goods)</u>

- የእቃዎች ግዢ  የምንለው ለግንባታ ስራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን እና መሳሪያዎችን ሊያቀረቡ ከሚችሉ ግለሰቦች/ድርጅቶች ግዢ ስንፈጽም ነው። በዚህ የግዢ አይነት ወቅት ግንባታውን የሚያከናውን የሰው ሃይል ባለቤቱ የራሱን ቅጥር ሰራተኞች በመጠቀም ወይም ከሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የአገልግሎት ግዢ ውል በመፈጸም ግንባታው ይከናወናል።

## 3.2.3 በማ.ፐ.ት አሰራር የፐሮጀክቶች ግንባታ ሊከናወንባቸው የሚችሉ አማራጮች

በማ.ፐ.ፐ አሰራር የውሀ ተቋማት ግንባታ ለማከናወን ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው የግንባታ ዘዴዎች ከዚህ በሚከተሉት አማራጮች ናቸው።

### 1. ለአርቴዢያን ወይም ለአርቴዢያን ማህበር የጉልበት ዋጋ ውል ብቻ በመስጠት (Labor Contract /Service contract to Artisans or their association)

- በዚህ አማራጭ ወቅት የግንባታ መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ዋ.ሽ.ኮው በግዢ እና/ወይም በውሰት (ከወረዳው የውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት) ያቀርባል።

### 2. ለአርቴዢያን ወይም ለአርቴዢያን ማህበር የጉልበት ስራውንና በወረዳ ደረጃ ሊገኙ የሚችሉ የግንባታ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን በግዢ በማቅረብ ግንባታውን እንዲያከናውኑ ውል በመስጠት።

- በዚህ አማራጭ ወቅት በአርቴዠያኑም ሆነ በማህበሩ ሊቀርቡ የማይችሉ የግንባታ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን ዋ.ሽ.ኮው በግዢ እና ወይም በውሰት (ከወረዳው የውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት) ያቀርባል።

## 3. የስራ ፈቃድ ላላቸው የግል ተቋራጮች ሙሉ ውል በመስጠት (Full contract to liscenced private contractors)

- በዚህ አማራጭ ወቅት በህብረተሰብ ተሳትፎ ከሚቀርቡት የሰው ሃይልና ግንባታ ቁሳቁሶች ውጭ ያሉ ለስራው የሚያስፈለጉ የሰው ሀይል፣ ግንባታ ቁሳቁስና መሳሪያዎችን በማቅረብ ግንባታውን እንዲከናውን ማድረግ ነው።
  - በዚህ አማራጭ ወቅት ጨረታ በማውጣትና በመምረጥ ህብረተሰቡ ተቋራጮቹችን በዋ.ሽ.ኮው አማካኝነት መቅጠር አለበት።

## 3.2.4 በማ.ፐ.ት አሰራር ልንጠቀምባቸው ለምንችለው የግንባታ አማራጭ ዘዴዎች ልንከተለው የሚገባ የግዢ ስርአት

በማ.ፐ.ት አሰራር የትግበራ ኡደት (Implementation Cycle) ወቅት ስለምንከተለው የግዢ ስርአት አንዳንድ ነጥቦችን ከማንሳታችን በፊት በማ.ፐ.ት የትግበራ መመሪያ ላይ ይህን በተመለከተ የተቀመጡ ዋና ዋና ነጥቦችን እንመልከት።

1. ለውሃ ተቋሙ ግንባታ ህብረተሰቡና የሱ ተወካዮች (የዋ.ሽ.ኮ አባላት) ሙሉ ሀላፊነቱን ይወስዳሉ። ይህም ከተቋራጮች እና ከአርቴዥያን ጋር ውል በመያዝ፣ የግንባታ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን በመግዛትና የአካባቢ ጉልበትንና ቁሳቁሶችን ማቅረብን ያጠቃልላል።

2. የወረዳው የልማት አጋሮች በተለይም የዉሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ዋ.ሽ.ኮው የግንባታ ስራን ሊያከናውን የሚችል አርቴዢያንም ሆነ የግል ተቋራጭ በሚመርጥበት ወቅት፣ እንዲሁም የግንባታ ቁሳቁሶችንም ሆነ መሳሪያዎችን ግዢ በራሱም ሆነ ግዢውን እንዲያከናውንለት ውል የሰጠው አርቴዢያን/ማህበር በሚያከናውንበት ወቅት ጥራታቸውን የጠበቁና ወቅታዊ የገበያ ዋጋን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ሞያዊ ምክር/ እገዛ የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው።

3. ህብረተሰቡ ለውሃ ጣቢያዎች ግንባታ የሚውሉ ቁሳቁሶችን፣ መሣሪያዎችንና አገልግሎቶችን የመግዛት ሙሉ ሀላፊነት አለበት። ነገር ግን የኮንክሪት ሲሊንደር ማምረቻ ሞልድ፣ የቧንቧ ጥርስ ማውጫያና ሌሎች የእጅ መሣሪያዎችን ከወረዳው የውሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ይዋሳሉ። እንዲሁም ዋ.ሽ.ኮው ቁሳቁሶችን ለማጓጓዝ ሊከራየው የሚችለው የግል መኪና ሊያገኝ ካልቻለ ወረዳው ቁሳቁሶችን የማጓጓዝ እገዛ ያደርጋል።

በማ.ፕ.ት የፕሮጀክት ትግበራ ወቅት ልንጠቀማቸው የሚችሉ የግንባታ አማራጭ ዘዴዎችን ከላይ በ 3.2.3 ላይ ጠቅለል ባለ መልኩ ለማስቀመጥ ተሞክረዋል፡፡

እነዚህን የግንባታ ዘዴዎች ተግባራዊ ለማድርግ ዋ.ሽ.ኮው የሚጠቀምበት የግዢ ስርአት ዝርዝር ሁኔታ ፣ የበጀት ጣሪያ እና ተዛማጅ ጉዳዮችን በተመለከተ የማ.ፕ.ት የግዢ አፈጻጸም ስርአት ( CMP Procurement Procedure) በሚለው መመሪያ ውስጥ ዝርዝሩ የተገለጸ ሁኖ ጠቅልል ባለ መልኩ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 3.2.4.1 የባለሙያ ቅጥር/ ግዢ

1. አርቴዢያን ወይም የአርቴዢያን ማህበርን የጉልበት ስራ ብቻ እንዲያከናውን ወይም ጉልበትና የተወሰኑ የግንባታ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን እንዲያቀርብ ውል በመያዝ ለማሰራት ሲፈለግ ጨረታ በማውጣት ወይም ከወረዳው የውሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ጋር በመመካከር ህብረተሰቡ በዋ.ሽ.ኮው አማካኝነት መቅጠር አለበት፡፡

2. በህብረተሰብ ተሳትፎ ከሚቀርቡት የሰው ሃይልና ግንባታ ቁሳቁሶች ውጭ ያሉ ለስራው የሚያስፈለጉ የሰው ሀይል፣ ግንባታ ቁሳቁስና መሳሪያዎችን በማቅረብ ግንባታው የስራ ፈቃድ ባላቸው የግል ተቋራጮች ሙሉ ውል (Full contract to liscenced private contractors) እንዲከናወን በምናስብበት ወቅት ለውሃ ተቋሙ ግንባታ አስፈላጊ የሆኑትን ተቋራጮች ጨረታ በማውጣትና በመምረጥ ህብረተሰቡ በዋ.ሽ.ኮው አማካኝነት መቅጠር አለበት፡፡ ተቋራጮች አመራረጥ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

### 3.2.4.2 የእቃዎች ግዢ

### 3.2.4.2.1 በወረዳ ደረጃ የሚገኙ እቃዎችን ዋ.ሽ.ኮው በግዢ ሲያቀርብ

በተቻለ መጠን ማንኛውም የግንባታ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች /አሸዋ፣ የወንዝ ጠጠር፣ ሰሚንቶ፣ ፌሮ፣ ቆርቆሮ፣ አካፋ፣ ዶማ፣ ባሊ፣ መዶሻ፣ ገመድ፣ የእጅ ፓምፕ ወዘተ.../ ለዚሁ የተቀረጸውን የግዢ አፈጻጸም ስርዓት (Procurement Procedure) በመከተል ዋ.ሽ.ኮው ግዢውን ይፈጽማል።

### 3.2.4.2.2 በአርቴዢያን ወይም በአርቴዢያን ማህበር የሚደረግ ግዢ

ሕብረተሰቡ የግንባታ ቁሳቁሶችን እና መሳሪያዎችን ለመግዛት አቅምና ጊዜ ከሌለው ለአርቴዥያኖች ወይም ለማህበራቸው ውል መስጠት ይችላል። በዚህም ወቅት አርቴዥያኖች/ማህበራቸው ከአገልግሎት ክፍያዎች ጋር የዕቃዎችን መግዣና ወደ ግንባታ ቦታው ማጓጓዣ ክፍያዎችን መጠየቅ አለባቸው። እንዲሁም ለግንባታ ቁሳቁሶች ጥራት ተጠያቂነት አለባቸው ይህም በውሉ ላይ መቀመጥ አለበት።

### 3.2.4.2.3 በወረዳው የሚደገፉ ግዥዎች

እንደየወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ የሚለያይ ሁኖ በወረዳው ውስጥ ያሉ አቅራቢዎች ማቅረብ ካልቻሉና በዋ.ሽ.ኮው ለመገዛት አስቸጋሪ ከሆነ የእጅ ፓምፕ የወረዳው ገንዘብና ፕላን ጽ/ቤት የመንግስት የግዢ ስርዓትን በመከተል ግዢውን በመፈጸም ዋ.ሽ.ኮዎች ፓምፖቹን ለስራ በሚፈለጉበት ወቅት ከወረዳው የውሀ ሃብት ልማት ጽ/ቤት መጋዘን ወጪ በማድረግ መውሰድ ይችላሉ። ይህ ሁኔታ መወሰነ ያለበት በእቅድ ዝግጅት ወቅት ነው። ምክንቱም ገንዘቡ የሚተላለፍበትን አማራጭ ለመወሰን (ለዋ.ሽ.ኮ.ው ወይስ ለወ.ገ.ፕ ጽ/ቤት) ነው።

### 3.2.4.2.4 ሌሎች የግንባታ መሳሪያዎችን አቅርቦት በተመለከተ

- ከዋጋቸውም አንጻርም ሆነ በአገልግሎት ዘመናቸው ለብዙ የውሀ ጣቢያዎች አገልግሎት ለመስጠት ከመቻላቸው አንጻር በአንድ የውሃ ጠቢያ ደረጃ ሊገዙ የማይችሉ የግንባታ መሳሪያዎችን ለምሳሌ ሲሊንደር ማምረቻ ሞልድ፣ የቧንቧ ጥርስ ማውጫ፣ የግንበኛ ማንኪያ፣ የቧንቧ መፍቻ፣ ቻየን ብሎክ ወዘተ...

የመሳሰሉትን ዋ.ሽ.ኮው ወይም አርቴዢያኑ ከወረዳው የውሀ ሀብት ልማት ጽ/ቤት አስፈላጊ በሚሆኑበት ወቅት ይዋሳል ፡፡

## 3.2.4.3 የግንባታ ቁሳቁሶችን እና መሳሪያዎችን ማጓጓዝ

ሁኔታዎች ስከተመቻቹ ድረስ በዋ.ሽ.ኮውም ሆነ በአርቴዢያኑ የግንባታ ቁሳቁሶች ግዢ ሲፈጸም እስከ ውሀ ጣቢያው ንዲደርሱ ይመረጣል፡፡ ነገር ግን ቁሳቁሶችን ለማጓጓዝ ግባብ ባለው የኪራይ ዋጋ የግል መጓጓዣ ማግኘት የማይቻል ከሆነ በተቻለው አማራጭ የወረዳው የውሀ ሃብት ልማት ጽ/ቤት እቃዎችንና መሳሪያዎችን በማጓጓዝ ትብብር ማድረግ አለበት፡፡

## 3.2.4.3 በማ.ፕ.ት የግዢ ስርአት ወቅት ከወረዳው ለዋ.ሽ.ኮው የሚሰጡ እገዛዎች

የወረዳው የልማት አጋሮች በተለይም የዉሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ዋ.ሽ.ኮው የሰው ሀይል/ተቋራጭ ቅጥርም ሆነ የግንባታ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች ግዢ በሚያከናውንበት ወቅት የሚከተሉትን እገዛዎች ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ዋ.ሽ.ኮው የሰው ሃይል ቅጥርም ሆነ የግንባታ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን ግዢ በተዘጋጀው የግዢ መመሪያ መሰረት እንዲያከናውን እገዛ ያደርጋል/ማከናወናቸውን ክትትል ያደርጋል፡፡
- ዋ.ሽ.ኮው የሰው ሀይል ቅጥርም ሆነ የቁሳቁስ እና የመሳሪያዎች ግዢ ለማከናወን አንዳንድ ዝግጅቶች በሚያደርግበት ወቅት ለምሳሌ የጨረታ ሰነድ ዝግጅት፣ አሸናፊውን ተቋራጭ በመለየት፣ የውል ሰነድ ዝግጅት ወቅት ወዘተ... ሞያዊ እገዛ ያደርጋል፡፡
- ዋ.ሽ.ኮው የግንባታ ቁሳቁሶችንም ሆነ መሳሪያዎችን ግዢ በራሱም ሆነ ግዢውን እንዲያከናውንለት ውል የሰጠው አርቴዢያን/ የአርቴዢያን ማህበር ግዢውን በሚያከናውንበት ወቅት ጥራታቸውን የጠበቁና ወቅታዊ የገበያ ዋጋን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ሞያዊ ምክር/ ገዛ/ ይሰጣል፡፡
- ዋ.ሽ.ኮው የግንባታ ስራን ሊያከናውን የሚችል አርቴዢያንም ሆነ የግል ተቋራጭ በሚመርጥበት ወቅት የሚመረጡት አርቴዢያኖችም ሆነ ተቋራጩ ብቃት ያላቸው እንዲሁም ዋጋቸው ከገበያ ዋጋ ጋር የተገናዘበ እንዲሆኑ ሞያዊ እገዛ ያደርጋል/ምክር ይሰጣል፡፡